# ቅደሚኝ



ታደለ ከያኔው
ሐምሌ ፪፣ ፳፻፲፬

“**ነይ እንሂድ**” ብዬ አመጣሁሽ እንጂ፣ የት እንደማደርስሽ ግን አላዉቅም:: ንገሪኝ፣ በየት በኩል እንሂድ? መንገድ ነዉ ብዬ ያሳየሁሽ ሁሉ አሁን ገደል ሆኗል:: የእኔ ነዉ ያልሁሽ ሁሉ ከእጄ ጠፍቷል:: ከእኛ ጋር ናቸዉ ያልሁሽ ሁሉ ሄደዉ ሄደዉ አልቀዋል:: ሌላዉስ ይቅር ግድ የለም:: እኔ በአንቺ እድሜ ሳለሁ ወደሄድሁበት ብወስድሽ፣ ማናችን እንደምንመለስ ማናችን ደግሞ እንደምናልፍ አላዉቀዉም:: የትራፊክ ፖሊሶችን ዓይነት እና ብዛት አትጠይቂኝ፤ አልነግርሽም:: ልንገርሽስ ስንቱን? ‹ተመለሱ› ይሉናል:: ‹እሺ› ብለን ወደመጣንበት ስንዞር ደግሞ ይመሽብናል:: ብንሄድም፣ ብንቆምም፣ ብንመለስም ያዉ ነዉ:: እኔስ የምይዝ የምጨብጠዉ ቸግሮኝ ነዉ:: እግዚአብሔር ግን ለምን ዝም አለ በማርያም? መመለስም ማሳለፍም የእሱ መሆኑን እያመንለት፣ ስራዉን ሲቀሙት እንዴት አስቻለዉ? ቆይ፤ በመንግሥትነቴ አትምጡብኝ ማለቱ ለምን ነበር?

ንገሪኝ:: በየት በኩል እንሂድ?

እንዲያዉም እንዲያዉም፣ ያለ እድሜሽ ይኼን ከነገርሁሽ አይቀር፣ ጨርሼ ልንገርሽ:: ልንገርሽ አይደል? ከእናትሽ እንጉርጉሮ ነዉ የሰማሁት:: እንግዲህ እሷ ዉሎዋ ከትላልቆቹ ጋር ስለሆነ፣ ከእነሱ ሳይሆን አይቀርም የሰማችዉ:: ብቻ ምን አለች?

**♬እግዜርን አግኝቼ እንዴት በነገርሁት**
**የደላኝ መሰለዉ ተመስገን ስላልሁት♬**

አለችልሻ!

የኋላ ኋላ ግን ተፀፀተች:: የልብሽን ስትቀምስ፣ ከእግዜር ጋር መዋቀሱን እርግፍ አድርጋ ተወችዉ:: ሙጥጥ ያለ ተስፋዋ እንደ አዲስ መነጨ:: አንቺን ከእሷ ጋር ሳይ እኔም እለወጣለሁ:: በራሴ ዓይኖች ባየሁ ጊዜ፣ የብራዉ መብረቅ ብልጭ ድርግም ሲል ብቻ እንጂ ሰማዩ እንኳን አልታየኝም:: በራሴ ጆሮ በሰማሁ ጊዜ፣ ወደኔ የተወረወረ ጦር እያፉጫጨ ሲመጣብኝ እንጂ ሌላ አልሰማሁም:: ባሸት - ቅርናት ቅርናት፣ ባስብ - ፍርሃት ፍርሃት፣ ብጓዝ - ድካም ድካም፣ ብቀምስ - ሬት ሬት፣ ብተኛም ቅዠት ብቻ ነበር የሚጫወትብኝ::

በአንቺ ልብ ሲሆን ግን ሌላ ነዉ::

ቅደሚኝ፤ እከተልሻለሁ:: ያጣሁትን ሁሉ አሳምረሽ እንደምትመልሺዉ ተማምኜብሻለሁ:: ያሸነፈኝን ሁሉ እንደምታሸንፊልኝ፣ በፈራሁት ፊት ሁሉ በልበ ሙሉነት እንደምታቆሚኝ አልጠራጠርም:: በአንቺ ጊዜ ፀሐይም ከፀሐይነቷ፣ ክረምትም ከክረምትነቱ፣ ሰማይም ሆነ ሌላ ሌላዉ ሁሉ ከቦታዉ ዝቅ እንደማይል ተስፋ አለኝ:: ስለሆነም ‹**ለምን አመጣሁሽ**› ብዬ ከራሴ ጋር መጣላቱን ትቼዋለሁ:: እንኳንም መጣሽልኝ::

መልካም ልደት

(መልካም እድል)